# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

**የዓቢይ ጾም ሰባተኛው ሰንበት «ኒቆዲሞስ» ይባላል።**

ስያሜው የቅዱስ ያሬድ ነው። በዚህ ዕለት የፈሪሳውያን አለቃ ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ጌታ መጥቶ ሲማር ጌታም ምስጢረ ጥምቀትን ዳግም ልደትን ለኒቆዲሞስ እንዳስተማረው እየጠቀሰ ቅዱስ ያሬድ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስት ላይ ያለውን ስለዘመረው የዕለቱ ስያሜ ኒቆዲሞስ ተብሏል።

## የዕለቱ ምስባክ

ሐውጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ
አመከርከኒ ወኢተረክበ አመጻ በላዕሌየ
ከመ ኢይንብብ አፉየ ግብረ ዕጓለእመሕያው

ልቤን ፈተንከው በሌሊትም ጎበኘኸኝ
ፈተንከኝ ምንም አላገኘህብኝም
የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው።

መዝ ፲፮፥፫

**ወንጌል፥ ዮሐ ፫፥፩-፳፩**
**ቅዳሴ፥ ቅዳሴ ማርያም**

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

«ሆረ ኀቤሁ ዘስሙ ኒቆዲሞስ»
«ኒቆዲሞስ የሚባለው ወደሱ ሄደ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፯፥፩-፲፱ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፬፥፲፰-ፍጻሜው | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፭፥፴፬-ፍጻሜው | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# ኒቆዲሞስ

ኒቆዲሞስ አዋቂና የአይሁድ መምህር ነበር (ዮሐ ፫፥፲)። መድኃኒታችን በቤተ መቅደስ ባደረገው ተአምራት ኒቆዲሞስ ተማርኮ ነበር (ዮሐ ፯፥፲፫-፳፫)። ኒቆዲሞስ ፈሪሳውያንን ፈርቶ የአይሁድ አለቃም ስለሆነ አይሁድ ከሚቃወሙት መሲህ ጋር ከታየ ሊቃወሙት ስለሚችሉ በሌሊት እንጂ በመአልት፤ በጨለማ እንጂ በቀን ወደ መሲህ መሄድ አልቻለም (ዮሐ ፫፥፩)። በመሆኑም በጨለማ ወደ ብርሃን ክርስቶስ መጣ። በኋላም በዕለተ ዐርብ ፀሐይ ሲጨልም ቀኑ በጨለማ ሲዋጥ የመሲህን ሥጋ ለመቅበር በጨለማ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሄድ እናያለን (ዮሐ ፲፱፥፴፱)። በማታ የተማረው ትምህርት ልቡን ነክቶት ነበርና የክርስቶስን ትምህርትና ተአምራት አይሁድ ሲቃወሙ እርሱ ክርስቶስን ይደግፍ ነበር (ዮሐ ፯፥፶፩)።

ኒቆዲሞስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ሊያነጋግረው ቀረበ። ምልክቶቹን ቢያምንም አምላክነቱን አልተቀበለም ነበር። ኒቆዲሞስ ትንቢተ ነቢያትን የማንበብ እድል የነበረው ሰው ሲሆን ክርስቶስ የሚያስተምረውን ትምህርት ለማመን ለመቀበል ባለመቻሉ ጌታችን «አንተ የአይሁድ መምህር ስትሆን ይህንን አታውቅም?» ብሎ አለማወቁን ገለጸ ወይም ውዳሴ ከዘለፋ ተናገረ። «የአይሁድ መምህር» ብሎ ውዳሴ፤ «ይህንን አታውቅም» ብሎ ዘለፋ ተናገረ። ባለማወቁም ተደነቀ፤ አምላክነቱንም መምህርነቱንም ገለጸለት (ዮሐ ፲፫፥፲፫-፲፬ ። ማቴ ፳፫፥፰)። መምህርና አምላክ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መድኃኔዓለም መሆኑንም ገለጸለት (ዮሐ ፫፥፪ ። ዮሐ ፫፥፲፬-፲፰)።

ኒቆዲሞስ በኦሪት የእርግማን ምልክት እንደሆነ በሚያውቀው መስቀልም በረከት እንደሚመጣ የነሐሱን እባብ ታሪክ ጠቅሶ መድኃኒታችን ተናገረ (ዘኁ ፳፩፥፰ ። ገላ ፫፥፲፫ ። ፪ኛ ቆሮ ፭፥፳፩ ። ዮሐ ፫፥፲፬-፲፭)። መድኃኒታችን ለኒቆዲሞስ ካስተማረው ትምህርት ውስጥ ኒቆዲሞስን ያስቸገረው ወይም የከበደው የሰው ልጅ ሁለተኛ መወለድ ያስፈልገዋል የሚለው ትምህርት ነበር። መድኃኒታችን ከሥጋ የተወለደ ሥጋ በመሆኑ ሰው ከመንፈስ መወለድ መቻል አለበት ብሎ በማስተማሩ ኒቆዲሞስ ከሚያውቀው ምድራዊ ልደት ጋር አመሳስሎ «ሰው ካደገ በኋላ እንዴት ከእናቱ ሊወለድ ይችላል?» አለው። ጌታ ግን «ከውሃና ከመንፈስ ትወለዱ ዘንድ አላችሁ» ብሎ በጥምቀት የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን ተናገረ።

መድኃኒታችን በወንጌል እንዳስተማረን መንግሥተ እግዚአብሔርን ለመውረስ ሁለተኛ መወለድ ግድ ያስፈልጋል። አንድ ሰው በሥጋ ከወላጆቹ ሳይወለድ በዚህ ዓለም መኖር እንደማይችል እንደዚሁ ከእግዚአብሔር ያልተወለደም በመንፈሳዊው ዓለም መኖር አይችልም። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ምሳሌ ቢፈጠርም በኃጢአት በመውደቁ፤ የሰይጣንን ሃሳብ በመቀበሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ቀርቶ የሰይጣን ልጅ ሆኖአል። ዘርም በምድር ላይ በሚተካበት ጊዜ የመጀመሪያውን ነፍሰ ገዳይ ድንጋይ ወርዋሪ ልጁን ቃየልን በነፍሰ ገዳዩ ዲያቢሎስ አምሳል (ዮሐ ፰፥፵፬-፵፭) ወልዶ ነበር። ሴትም ቢሆን ከመንፈሳዊው ምውት አዳም በመወለዱ ምውት ነበር። የአዳም ልጅ ሁሉ በአዳም ከሞት ሥር የወደቀ መዋቲ በመሆኑ በሕይወት ለሕይወት ለመኖር የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ በወንጌል በጥምቀት በእምነት ከእግዚአብሔር መወለድ ግድ ነው።

አንባቢ ሆይ፥ ሁለተኛ መወለድ የአሮጌውን ሰው ጠባይና ባህርይ መጣል አዲሱን ሰው ክርስቶስን መልበስ ግድ ነውና አዳማዊ ደካማ ባሕርይን በቃሉ ሻር። ከእርሱ ተወለድ። ርስቱን ትወርስ ዘንድ ልጅ ሁን፤ እግዚአብሔር ልጅ ትሆን ዘንድ ጠርቶሃልና። ተወልደህም ከሆነ ልጅነትህን አታባክነው፤ አባትህን መስለህ ኑር። አባቱን የማይመስል ልጅ አጠራጣሪ ነውና በሁለንተናህ አባትህን ምሰለው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

ከመምህር ልዑል ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM